# ታሪኩን የረሳ ሀገሩን ይቀማል

አሜሪካ የጉድ ሀገር እንዲሉ በአንድ በኩል ጥቁር አሜሪካዊን ለፕሬዚዳንትነት ልታበቃ ነው ስትባል በሌላ በኩል ደግሞ ድርጊቶቿ ሁሉ ለብዙሀኑ የዓለም ሕዝብ አልበጅ ብሎ ሲያስወግዛት ይታያል፡፡ ታዲያ ሞኝ በርክቷልና አሜሪካ ነፃ ታወጣናለች ወይም ትታደገናለችና እንለምናት፤እንፀልይላት የሚሉም የራሳችን ወገኖች አልጠፉም፡፡ በዚች የጉድ ሀገር ደግሞ ባለፈው ሰሞን በተካሄደው የኢትዮጵያውያን ሰሜን አሜሪካ የእግር ኳስ ውድድር ላይ ወንጀልን አዳናቂ ግለሰብ የዚያን ስመ ጥፉ ግብረ አረመኔ መንግስቱ ኃይለማርያምን ምስል የያዙ ከናቴራዎች ሲሸጥ መገኘቱ ብቻ ሳይሆን አንዱ ይባስ ብሎ ይህንኑ ከናቴራ ለብሶ ሲንገዋለል ታይቷል፡፡ ወንድም  እህት በቀይ ሽብር ያለቁበት፤ አባት እናቱ በፋሺስቱ ደርግ የተጨፈጨፉበት አንድም በቦታው ያልነበር ይመስል ይህንን ባለጌ ግለሰብና አላፍር ያለውን ወንጀል አጃቢ ከናቴራ ሻጭ አልበዛም ወይ ያላቸው አልተገኘም፡፡ መቻቻል ወንጀልንና ወንጀለኛን መቻል ሆኖ ይሆን?

ወደ ቁም ነገሩ ስንገባ ታሪክን መርሳት ራስን ለውርደትና ለጭቆና ማጋለጥ ከመሆኑ ሌላ ሀገርንም ሊያስቀማ ይችላል፡፡ ገና 17 ዓመት በማለፉ ብቻ፤ ያውም ያን የግፍ ዘመን የኖሩ ሞተው ሳያልቁ የቀይ ሽብርን መከራ ሊክዱ ወይም ቀራርፈው ሊያሳንሱ የሚጥሩ በርክተዋል፡፡ በዚያ የግፍ ዘመን ላይ በማተኮር ከዛሬው ሰይጣን ላይ ዕይታችን ትኩረታችን እንዳይነሳ ብንሻም የዚያ ዘመን ወንጀለኞች ነጋ ጠባ ታሪክን ሊበራርዙ መሞከራቸው ያለ ነውና በየጊዜው ለታሪክና ለሀቅ ዋርዲያ መውጣቱ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀውና ሊያውቀውም የሚገባ ሀቅ መንግስቱ ኃይለማርያምና አገዛዙ የኢትዮጵያን አንድ ትውልድ የጨፈጨፈና ሀገሪቷን ለወያኔ አጋልጦ የሰጠ በታሪክ ዘወትር የሚወገዝ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ነው አረመኔው በደረት ተለጥፎና ተሞግሶ ሲሄድ ደም ረጋጭ ወንጀለኞች በዚህም መንገድ፤ የሀሰት ታሪክ በመፃፍም ሆነ በመለፈፍ ታሪካችንን እያበላሹና እየሰረዙት ነውና ጎበዝ ምነዋ ወንጀልን መቻል በዛሳ ማለቱ የግድ የሆነብን፡፡

ታሪክን ስንዘክር አንድም ያለፍነውን ሂደት ለመረዳትና ሀገራችንን በመስዋዕትነት ያቆዩልንንም  ለማክበር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሀገርን ጠላቶች ወዳጅ ከማለት ስህተት ራስን ለማዳን የግድ ታሪካችንን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከበራዦችና ከላሾችም መከላከል ያስፈልገናል፡፡ አፄ ኃይለስላሴ ከራሳቸው ስልጣን ፍላጎት የተነሳ የጣሊያን ወረራን የተዋጉትን አርበኞች ሳይሆን ባንዳውንና መሰል ከሀዲውን ቅድሚያና ቦታ በመስጠታቸው የተከፈለው መስዋዕትነትና ለኢትዮጵያ መስዋዕት የሆኑት ጀግኖች ስማቸውም ሳይጠቀስ ቀርቷል፡፡ እነ ዕጌ ማርቆስ፤ዮሴፍ ወርቅነህ፤ ዮሐንስ ቦሩ፤ ተክለ ብርሃን፤ ደበበ ገብሩ፤አሰፋ

ተድላ፤አብርሃም ደቦጭ፤ዘርዓይ ደረስ ዓይነቶቹ ወጣት አርበኞች አልፎ አልፎ ስማቸው ቢነሳም ሰንቶቹ ተረስተዋል፡፡ ይህ የታሪክ ዳምጠው ሀቁን ደፍጥጦ ሲያልፍና ደብዛ ሲያጠፋ በዝምታ በመታለፉ የባንዳ ታሪክ ገኖ፤የጣሊያን ተሿሚ ቦታ ይዞ ባጅቷል፡፡ ባንዳ ራሱን አርበኛ እያደረገም ለሹመት በቅቷል፡፡ ይህ በመለመዱ ለለውጥ ተነስተናል ያሉ ክፍሎችም የትግላቸውን መርህ ገብር ከሀሰት ታሪክ ጋር አጣምረው አቅርበዋል፡፡ ኢሕአፓ የኤርትራ ጥያቄ በሰላምና በዴሞክራሲ ይፈታ ብሎ ቢቆምም ይህ አቅዋሙ ለግንባሮቹ አላጠግብ ብሏቸው ኋላም ከወያኔም አብረው ኢሕአፓን የወጉት ኤርትራ የኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ናት ያሉትን መሰረተ ቢስና ኢታሪካዊ አቅዋም አልቀበል በማለቱ ነው፡፡ ኦነግም ቢሆን ከሀቅ የተጣላ “የኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለም ” የሚለውን አቅዋሙን ኢሕአፓ ባለመቀበሉ ድርጅቱን ሲኮንን ቆይቷል፡፡ ወያኔም የትግራይን መገንጠል ሲገፋ የፃፈው የሀሰት ታሪክ ተደጋግሞ የተነገረ ነው፡፡ የሀሰት ታሪክን የእውነት አስመስሎ ሲያቀርቡ ዝም ከተባለ በዚሁ መሰረት ሀገርን ያፈርሳሉ፤ ቅርስን አፈር ያበላሉ፡፡ ኢሕአፓ ትምክህተኛ፤ አባይ ኢትዮጵያ፤ አማራ ነፍጠኛ ወዘተ የተባለው የሀገራችንን ታሪክ አላስደፈር አላስቀይር ስላለ መሆኑ ደግሞ የሚታወቅ ነው፡፡

ወያኔ ነጋ ጠባ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚበራርዘው ለጥፋት ተልዕኮው ይህ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ የብዙ ሺ ዓመት ታሪክ ያለትን ሀገር የመቶ ዓመት ማለቱ ለግንጠላና ፍርሻው እንዲያመቸው ነው፡፡ በሰንደቅ ዓላማ ያላገጠውና በመጨረሻም የቀየረውም ታሪክን ሊያስረሳ ብሎ ነው፡፡ ሕዝብን ለመከፋፈል ስለተነሳ የአንድነትን ሳይሆን የቁርሾን ታሪክ በራሱ ፅፎ ይጎነጉናል፡፡ የወያኔ ቡድን በሀገር ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለመደበቅ አዲስ ታሪክ ይፅፋል፡፡ ሀገር አጥፊ ሆኖ ሳለ ለሀገር የቆመ ይመስል የቡድኑን የጦር መሪ ምስል ከአፄ ቴድሮስ፤ ዮሐንስና ምኒሊክ ምስሎች ጎን ለጥፎ እንደነበርም ይታወሳል፡፡ በሆዱ ያባውን አውጥቶ በአክሱም ሀውልት ምን አገባችሁ ያላለንን ያህል ዛሬ ደግሞ ከጣሊያን የመጣ ሀውልት አለና ሀገር ሙሉ ይኩራ ሊል ሲቃጣ መታዘብ ሲያንስ ነው፡፡ ወያኔ በኦጋዴን ጦርነት ወቅት የዚያድ ባሬን ወረራ ደግፎ እንደነበር ለመሸፈን የደርግን ቅጥፈት በማስተጋባት የራሱን ጥፋት በኢሕአፓ ሊያላክክ ሞክሯል፡፡ የወያኔ በሬ ወለደ የታወቀ ቢሆንም በታሪክ ብረዛው የተለይ አደጋ የሚሆነው ወጣቱን ወይም አዲሱን ትውልድ ለመበከል የታቀደ መሆኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት እንዳልኖረና ሀገሩንም በጋራ ትግል እንዳላስከበረ አስመሰሎ የወያኔ ቡድን ክፍፍልና ግጭት ቀስቃሽ የሀሰት ታሪክ ይተርካል፡፡ የፈረደበት የአማራ ሕዝብንም በበዳይነት መድቦ ሊያስጠላ ይፍጨረጨራል፡፡ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተገናኝተውና አብረው ለሀገራቸው እንዳይቆሙ የብሄረሰብና የሀይማኖት ግምብ በመሀላቸው አቁሞ ድሮም አልተገናኛችሁ ዛሬም አትገናኙ ቅስቀሳውን ያስፋፋል፡፡ የወያኔ ታሪክ ተረት ተረት ቢባልም እንኳን ከሀቅ ርቀቱ ከከዋክብት የመጠቀ ነው፡፡

ታሪክ ቅርስ ነው፡፡ ታሪክ ጋሻ ነው፡፡ ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ አለበት፡፡ ትውልድ የማንነቱ መሰረቱ ታሪኩ መሆን አለበት፡፡ የኢትዮጵያውያን የጋራ ታሪካቸው-- ፀጋውም ሆነ መደገም የሌለበት ክስተት- የጋራ ቅርሳቸው ሆኖ የጋራ ግንዛቤና ማንነታቸውንም የሚገልፅ ይሆናል፡፡ አንድ ሕዝብ የሚያሰኛቸውም ይኸው ነው፡፡ የብሄረሰብ ስብጥር ቢኖርም ኢትዮጵያውያን ከብሄረሰባቸው በፊትና ባሻገርም ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ መለስ ዜናዊና መሰሎቹ በቅድሚያ የሚገልፀን ትግሬ መሆናችን ነው ሲሉ ጠባብነታቸውን ይፋ ያደርጋሉ፡፡ መኩራራታቸው ደግሞ ምንኛ ግብዞችና መሀይሞች መሆናቸውን ያጋልጥባቸዋል፡፡ ይህ ግን ለእነሱ የሚገባቸው ወይም የሚጨንቃቸው ጉዳይ አይደለም፡፡ የሀሰት ታሪክን በማሰራጨት ድርጅትን ማስጠላት፤ የሀገርን ቅርስ ማክቸልቸል፤ አዲሱን ትውልድ ማናጋትና በተሳሳተ ቅኝት ማስኬድ የወያኔ ቡድን ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በተለይ ማንነቱን በሚያውቁትና ርኩስ ዓላማውን ሊያጋልጡ በሚችሉ ድርጅቶች ላይ አምርሮ ይዘምታል፡፡ ኢሕአፓን ከተመለከትን ወያኔ ገና ሲመሰረት ጀምሮ ጠላት ብሎ የተነሳበት ደርጅት ነው፡፡ የወያኔ የግንጠላና ፀረ አማራ ፀረ ኢትዮጵያ ጠባብ መርሀ ግብር በኢሕአፓ ስለተጋለጠና ኢሕአፓም ህብረ ብሄር ሆኖ ለሚታገሉ ሁሉ መሳባሰቢያና ኢትዮጵያዊ ቤት በመሆኑም የጠባቦቹ ዓይን ቀላ፡፡ ተባብረውም ኢሕአፓን መውጋት ብቻ ሳይሆን በድርጅቱ ላይ ይህ ነው የማይባል የሀሰት ዘመቻ አወረዱበት፡፡ ውሸት ሲደጋገም የሆነባቸው አንዳንዶች ዛሬ የወያኔና የደርግንም የሀሰት ፕሮፓጋንዳ መቆርፎድ ሲገባው ዋጋ ሊሰጡ ሲያለፉት እየታዘብን ነው፡፡ የኢሕአፓን አቅዋሞች አዛብተው ከማቅረብ ሌላ፤ያላደረ ገውን አድርጎ ነበር እያሉ፤ የቀይ ሽብርም ሰለባ ሆኖ እያለ ሽብርተኛ ብለው ሊከሱ እየጣሩ፤ ወያኔን በመቃወሙ ፀረ ትግሬ ነው እያሉ፤ ወዘተ ሲጮኹ እያዳመጥን ነው፡፡ የወያኔ ቅጥረኞች ስማቸውን እየቀየሩ፤ተልዕኮአቸውን ደብቀው በአፍ፤ በፅሁፍ፤በድረ ገፅ ወዘተ የተፋፋመ ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻ እያካሄዱ ያሉት አለምክንያት አይደለም፡፡ የወያኔን የሀሰት ታሪክ ኢሕአፓ ስለሚያጋልጥና ወያኔንም ሳያወላውል ስለሚታገል ነው፡፡ በዋሾዎች መንደር ሀቅን መቅበር ሰርግ ነው፡፡

እያንዳንዱ ዜጋ የታሪክ ዘብ ሆኖ መቆሙ ትልቅ ግዳጅ ነው፡፡ ታሪካችን የግድ ሆኖ ብዙውን ጊዜ መስዋዕትነትንና የዜጋ ደምን እንደ ቀለም ወስዶ የተፃፈ ነው፡፡ ይህ ከንቱ ወይም መና ሊቀር አይታሰብም፡፡ ኢትዮጵያ ወይ ሞት ብለው የተሰዉት አርበኞች ሁሉ ተረስተው ታሪክ የባንዳዎች ልትሆን መፍቀድ የለብንም፡፡ ፋሺስቱን ደርግ ሲታገሉ የተሰዉት ብዙ ሺ ጀግኖች ተረስተው ወንጀለኞቹ ጀግኖች ባለታሪኮች ሲባሉና ሲወደሱና ይባስ ብለውም ሰለባቸውን ዳግም በታሪክ ብረዛ ሊገድሉ ሲነሱ በዝምታ ልናልፈውም አይጠበቅም፡፡ ታሪካችን ቅርሳችን ነው፡፡ጋሻችን ነው፡፡ ማንነታችንን ገላጭ ነውናም አሳልፈን

**አንሰጠውም:: ይህን የምንለው ዛረን ነግ ለሚጠብቀን ትግል ወሳኝ በመሆኑ ነው:: በጋራ ለመታገል የጋራ ቅርሳችንን፤ታሪካችንን ማወቅ አለብን:: ያያዘንን ማወቅ ይገባናል:: ይህ ደግሞ ማን ጠላት ማን ወዳጅ መሆኑን ይገልፅልናል:: በሀገር ውስጥም ሆነ በባዕድ ሀገራችንን ማን በጠላትነት ሊያጠቃት ቆሞ እንደነበርና ዛረረም እንዳሰፈሰፈ ማወቅ ያስችለናል:: ታሪክ ካልተረሳ ያለፈ ስህተት አይደገምም:: ሕዝብ በትግል ሲሰማራ የደም ዋጋ ከፍሎ የተቀሰመው ትምህርትም ባዶ አይቀርም:: የሩቁን እንኳን ብንተው የግንቦት 97ኡ መርጫ ብዙ ትምህርት ለግሷል:: ያ ታሪካዊ እንቅስቃሴና የተከተለውም ሁኔታ አያሌ ትምህርትን ሰጥቶናል:: ያ ካልተረሳ በስተቀረ ዛሬም በወያነ ምርጫ ለመግባት ደፋ ቀና ከቶም የሚታይ አይሆንም:: ታሪክ ከተረሳ ግን ስህተትን መድገም አይቀሬ ይሆናል:: ለፌደራል ሰለባ፤ ለወያኔ መጫወቻ መሆን አይቀርም ማለት ነው::**

ታሪካችንን እንወቅ:: ታሪክ በገዮችን ነቅተን እንታገላቸው:: ቅርሳችንን ጋሻችንን እንጠብቅ::